የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

# የክርስትና ሕይወት መርሖዎች

## የመሪዎች መመሪያ

# የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ

## ትምሕርት 1፥ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

## መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀ መዝሙርነት መርሖዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም "የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ" የሚል ነዉ። የዚህ ተከታታይ ትምሕርቶችን ያቀፈው ክፍል ዓላማ፣ ተሳታፊዎች ወንጌልን በብቃት ለሌሎች በማካፈል (በማሠራጨት) ዉጤታማ እንዲሆኑ፣ ማስታጠቅና ማዘጋጀት ነዉ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት (ለሚኒስትሪ) እንዴት እንደሚያስታጥቀን መረዳት፤ የወንጌል መልእክታችንን፥ ለተለያዩ የዓለም እይታ ወይም አመለካከቶች እንዴት እንደምናዘጋጅ እናስተዉላለን። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ዉስጥ የተገኘዉንና፤ የማይለወጠዉን የተስፋ መልእክት፥ ወይም የምሥራች ቃል፤አሁንም ገና ክርስቶስን ወደ አላወቀዉ ዓለም እንድናመጣ ይረዳናል።

## የታለመለት ተጠቃሚ

የእነዚህ ትምሕርቶች ተጠቃሚ የሚሆኑት፡- ወንጌልን ይዘዉ ለመዉጣት የሚዘገጃጁ እና ቀድመዉም በወንጌል ሥርጭት አገልግሎት ላይ የተሰማሩት ናቸዉ። ይህ መድብል በተለይም ወንጌልን ይዘዉ፣ በተለያዩ ሀገሮችና ባሕሎች ማካከል ለሚመላለሱ አገልጋዮችና ሚኒስትሪዎች እጅግ ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ትምሕርቱ፥ በተለያዩ የዓለም እይታዎች አዉድ ዉስጥ፣ ሊሠራባቸዉ የሚችሉ መጠነ ሰፊ መረጃዎችን አካትቷል። እንደ እነዚህ ትምሕርቶች ምልከታ፣ ተሳታፊዎች አስቀድመዉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የወሰኑና፤ ክርስትናን የበለጠ በጥልቀት ለማጥናት የተነሳሱ ናቸዉ።

**የመሪዎች መመሪያ ዓላማ፡-** የትምሕርቱ መሪ ወይም አስተማሪ፣ ትምሕርቶችን ስታዘጋጅ አንተን ለመርዳት ነዉ። እነዚህን ትምሕርቶችና ቢጋሮች ከሌሎች "የደቀመዝሙርነት መርሖዎች" ማቴሪያሎች ጋራ በጥምረት መጠቀም ይቻላል። በድረ-ገፃችን፡ www.DEamharic.org ይመልከቱ።

---

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድተዉ የታተሙ ናቸዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.

# የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ
## ትምሕርት 1፥ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

### ዓላማ

የዚህ ትምሕርት ዓላማ፡- ተሳታፊዎች በወንጌል ሥርጭት አማካይነት የዓለምን ምርኮ ለክርስቶስ እንዲያመጡ፤ እንድሁም እስከ አሁንም በጌታ ላላመኑት ወንጌልን የሚመሰክሩባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያመቻቹ፣ ፍላጎታቸዉን ለመቀስቀስና ለማበረታታት ነዉ።

### የመሪዎች ማስታወሻ

ሁሉም ክርስቲያኖች ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንዲያካፍሉ ታዝዘዋል፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች እያንዳንዳቸዉ ፤ይህን ትዕዛዝ እዉን የሚያደርጉባቸዉ፤ የተለያየ ዕድልና ችሎታ አሏቸዉ። በተሳታፊዎች ወይም ተማሪዎች ቡድን ዉስጥ፣ በወንጌል ሥርጭት አገልግሎት ልምድ ያላቸዉ፤ በሌላ ወገን ደግሞ፥ ይህ ሃሳብ አዲስ የሆነባቸዉ፤ በተለይም በእምነታቸዉ ገና ጨቅላ የሆኑትም ለኖሩህ ይችላሉ። የዚህ ትምሕርት ትኩረት መሆን ያለበት፡-የሰዉ ልጅ ዓላማዉ፣ በሕይወቱና በ አገልግሎቱ ዉስጥ የእግዚአብሔርን ዓላማ መሻትና ማግኘት፤ ከዚያም፥ ከእርሱ ጋራ ኅብረት አድርጎ በመሳተፍ፣ ከፍፃሜ ማድረስ ነዉ።

## መግቢያ

**ከሚቀጥሉት ጥያቄዎች መካከል፥ ሁለት ወይም ሦስቱን መርጠህ፥ የቡድኑን አባላት ጠይቃቸዉ።**

- ❖*አንተን ቀርቦ፣ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንድትመጣ፣ የረዳህ ሰዉ ነበረ? ለመሆኑ አንድ ሰዉ ወንጌልን መስክሮልህ ያዉቃልን? ይህ ከሆነ፥ የክንዋኔዉ አኳኋን ምን ይመስል ነበረ?*

- ❖*ወንጌልን ለሌላ ሰዉ ለመመስከር ዕድል አግኝተህ ታዉቃለህ?*

- ❖*በሆነ አጋጣሚ፥ አንድ ሰዉ፡- "በዚህ ዓለም ዉስጥ የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድን ነዉ" ብሎ ቢጠይቅህ፣ ምን ብለህ ታረዳለህ?*

- ❖*እንደ ኢየሱስ አማኝ፣ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገዉ ወይም፣ የሚጠብቅብህ ምንድን ነዉ ብለህ ታስባለህ?*

## ጥናት

በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ ለቡድኑ በቂ ትምሕርት ስጥ:-

# ትምሕርት

❖1ኛ ቆሮንቶስ 10:31 ዉስጥ ጳዉሎስ በትክክል እንዲህ ይላል:- "እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" እንደ አማኝ ክርስቲያን፥ ዓለማዊዉ ወይም መንፈሳዊ ያለሆነዉ የዚህ ምድር ዕለት ከዕለት ኑሮህ፤ ከክርስትናዉ ጥሪህ የተገለለ እንደሆነ በማሰብ፣ ሕይወትህን ልትከፋፍለዉ አትችልም። በሁሉም የሕይወታችን ገፅታዎች፥ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ እንድናደርገዉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ስለዚህም የሕይወትህ ዓላማ፣ የእግዚአብሔርን ክብር ማወጅ፤ ሉአላዊነቱና መልኩ፣ በአንደበትህና በድርጊቶችህ፣ በሁለንተናዊ ሕይወትህ ጎልቶ እንዲታይ ማድረግ ነዉ።

➢በዚህ ዓለም ላይ (ዉስጥ)፣ የእግዚአብሔር ቀዳሚ ዓላማ ምን እንደሆነ እንድትደርስበትና እንድታስተዉል፤የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ:-

○ሉቃስ 19:10

○ሮሜ 10:9 እና 10

❖ተሳታፊዎች የሚቀጥሉትን ጥቅሶች አንብበዉ፤ ስለ ሰዉ ልጅ ዓላማ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል፥ አጥንተዉ እንዲደርሱበት አዘጋጃቸዉ። በእነዚህ ጥቅሶች ዉስጥ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቁልፍ ትእዛዛት ምንድን ናቸዉ?

○1ኛ ቆሮንቶስ 10:31

○ማቴዎስ 28:16-20

❖ይህንን በራሳችን ብርታት ብቻ እንድንፈፅመዉ እግዚአብሔር አይጠብቅብንም! ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበዉ፣ እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ሕይወታችንን እንዴት እንደሚያስታጥቀን ይወያዩ:-

○ኤፌሶን 4:11-16

○ዮሐንስ 15:5

○ሐዋርያት 1:8

❖ለመሆኑ የእኔ ዓላማ ምንድን ነዉ? የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ከሆንክ፤ ዓላማህ ተገልጦልሃል። እሱም ክብርን ለእግዚአብሔር ማምጣት፣ በእቅዱም መሳተፍና መታዘዝ ነዉ። የእግዚአብሔር እቅድ፥ ቀዳሚዉ ቤዛነቱ ሲሆን፤ባሕርያቱን እና ጎልወቱን:- ማለትም ፍቅሩን፥ ፀጋዉን እና፥ ምሕረቱን ገልጦ ማሳየት ነዉ። ይሁን እንጂ፥ ዓላማችን መሆን ስለሚገባዉ እዉነታ፥ የሰዉ ልጅ ያለዉ እይታ እጅግ የተለየ ነዉ።

➢ሉቃስ 12:16-20 አንብብ። ይህ ምሳሌ፥ በዓለም እቅድ እና፣ በእግዚአብሔር እቅድ መካከል፣ ስለ አለዉ ልዩነት ምን ይነግረናል? ዓለም በአብዛኛዉ የተያዘበትና የሚያሳስበዉ ምንድን ነዉ? እግዚአብሔርንስ ይበልጡን የሚያሳስበዉና የሚያስጨንቀዉ ምንድን ነዉ?

➢የግዚአብሔርን ፈቃድ ለማከናወን፥ የራሳችንን ፍላጎቶችና ቀዳሚ ነገሮቻችንን፣ የላቁ እና አስፈላጊ የሆኑ የእግዚአብሔር ሃሳቦች ጋራ ማጣጣም ያስፈልገናል።

# የዉይይት ጥያቄዎች

❖እግዚአብሔር ለአንተ ሕይወት ያለዉ ዓላማ፣ ከአንተ ዓላማ ጋራ የሚጣጣመዉ እንዴት ነዉ? ሁለቱን ዓላማዎች ለማቀናጀትስ ምን ማድረግ ትችላለህ?

❖ስለ ወንጌል ሥርጭት እና የጠፉትን ስለ መድረስ፣ ያለህ ግላዊ አመለካከት ምን ይመስላል? ሰዎችን ቀርበህ ስለ ኢየሱስ በማነጋገር፣ እምነታቸዉን በእርሱ ላይ የማድረግን አስፈላጊነት እንዴት ትገልፅላቸዋለህ?

❖ለሌሎች ሰዎች በመመስከር ተልእኮ ወቅት የሚያጋጥሙህን ተግዳሮቶች ምትወጣዉ እንዴት ነዉ?

❖ከእግዚአብሔር ጋራ በትክክል ለመራመድ የሚያበቃህ እድገት ላይ ለመድረስ ምን ታደርጋለህ?

# ፀሎት

ማቴዎስ 9:35-38 ለቡድኑ ወይም ለተሳታፊዎች ድምፅህን ከፍ አድርገህ አንብብላቸዉ። ትምሕርቱንም በፀሎት አጠናቅቀዉ። ልክ ክርስቶስ እንደ አደረገዉ፣ በርኅራኄ እንድንነሳሳና፣ የጠፉትን ለመፈለግ እንድንንቀሳቀስ ፀልዩ። የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን ወደ እርሻዉ እንዲልክ፤ እኛም መለኮታዊ ድፍረትን ተጎናፅፈን፣በወንጌል አርበኝነት፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተከትለን፥ ወንጌልን እንድናሰራጭ በርትታችሁ ፀልዩ። ተሳታፊዎች በዚህ ትምሕርት የዉይይት ክፍለ ጊዜዎች፣ በአካፈሏቸዉ ችግሮችና ተግዳሮቶች ላይ በየግላቸዉ ፀልዩላቸዉ።